# ከሚስጥሩ ባሻገር

## ልዋም ዓለም

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተመድ) በዓለም ላይ የሚታየውን የድህነት ሁኔታ በግማሽ ለመቀነስ በአውሮፓዊያኑ የዘመን አቆጣጠር በ2000 አንድ ሰፊ የልማት ፕሮግራም ይፋ አድርጓል፡፡ የምእተ ዓመቱ የልማት ግብ በሚል የተቀየሰው ይህ የልማት ፕሮግራም ለመተግበርና የተያዙትን ውጥኖች ለማሳካት የተሰጠው ጊዜ ደግሞ 15 ዓመት ነው፡፡ እናም በአሁኑ ወቅት የፕሮግራሙ የትግበራ ጊዜ ሊያበቃ የቀረው ሶስት ዓመት ያህል ብቻ ነው፡፡ እንዲያም ሆኖ ግን የዓለም አገራት ፕሮግራሙን በተያዘለት የጊዜ ገደብ አያሳኩም የሚል ግምገማ ከተለያዩ የሚመለከታቸው ክፍሎች በመቅረብ ላይ ነው፡፡

የልማት ግቡን በተመለከተ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ባካሄዷቸው ጥናቶች አገራት የልማት ግቦቹን በተያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ አያሳኩም የሚል ስጋት እንዳላቸው ጠቁመዋል፡፡ መንግስታትም ለፕሮግራሙ የሰጡት ትኩረት አናሳ መሆን ግቡ እንዳይሳካ አድርጓል ሲሉ እነዚሁ አካላት ያካሄዷቸው ጥናቶች በማረጋገጥ ላይ ናቸው፡፡ ፕሮግራሙ የሚመለከታቸው የዓለም አገራት የልማት እቅዶቻቸውን ድህነት ተኮር በማድረግ በከፍተኛ ቁርጠኝነት አለመንቀሳቀሳቸውም ለግቦቹ በጊዜው አለመተግበር ሌላ ምክንያት መሆኑም በብዙዎች የሚነገር እውነት ነው፡፡

የሆነው ሆኖ የልማት ግቡ የትግበራ ጊዜ ሶስት ዓመታት ቀርተውታል፡፡ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ የተወሰነ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ አንዳንድ አገራት ሊኖሩ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ብዙም አዎንታዊ ውጤት እንደማይጠበቅ በልማት ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ይናገራሉ፡፡

እንዲያም ሆኖ ጥቂት የሚባሉ የዓለም አገራት የልማት ፕሮግራሙን ለማሳካት እየተቃረቡ መሆናቸውንም ፕሮግራሙን በቅርብ የሚከታተለው የመንግስታቱ ድርጅት አስታውቋል፡፡ ከእነዚህ ጥቂት አገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ናት፡፡

ኢትዮጵያ በምእተ ዓመቱ የልማት ግብ ውስጥ የተካተቱትን ዋና ዋና የማህበራዊ ልማት ዘርፎችን በሚያስደንቅ ሁኔታ እያሻሻለች መሆኑን በዓለም አቀፍ ደረጃ የተካሄዱ አያሌ ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡ የአገሪቱ የልማት አጋር የሆኑ አገራትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶችም ይህንኑ በተጨባጭ በማረጋገጥ ለአገሪቱ የሚሰጡትን ድጋፍ አጠናክረው እንደሚቀጥሉ በመግለፅ ላይ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት የምእተ ዓመቱን የልማት ግቦች መሰረት በማድረግ በተለይ ባለፉት 10 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ስራ ላይ ባዋላቸው የልማት ፕሮግራሞች በትምህርት፣ በጤና፣ በምግብ ዋስትናና ሌሎች መሰል ዘርፎች ከፍተኛ እድገት ማሳየት መቻሉን የመንግስታቱ ድርጅት የስራ ኃላፊዎችና የልማት አጋር የሆኑ አገራት በተለያዩ አጋጣሚዎች ገልፀዋል፡፡

በተለይ የምእተ ዓመቱን የልማት ግቦች ትግበራና ውጤት የሚከታተለው የተመድ አካል (MDG Monitor) እንዳለው ኢትዮጵያ ስር የሰደደ ድህነትን ማስወገድ፣ ርሃብን መከላከል፣ የህጻናት ሞትን መቀነስንና የእናቶችን የጤና ሁኔታ ማሻሻልን ጨምሮ ከስምንቱ የልማት ግቦች አብዛኛውን ለማሳካት የሚያስችላትን ጎዳና በትክክል ይዛ በመጓዝ ላይ ናት፡፡

እነዚህ አካላት ወደአገሪቱ ጎራ በማለት ባካሄዷቸው ጉብኝቶችም ሆነ ጥናቶች የአገሪቱ የጤና አገልግሎት ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ ማደጉን፣ አብዛኛውን ህብረተሰብ የሚያጠቁ በሽታዎች መቀነሳቸውን አረጋግጠዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ከ80 ሚሊዮን በላይ የሆነው ኢትዮጵያ ህዝብ በየደጁ የጤና አገልግሎት መስጫዎች ተገንብተውለታል፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የጤና ባለሙያ በየገጠር መንደሮች ተሰማርተው መሰረታዊ የሆኑ የጤና አጠባበቅ ትምህርቶችንና አገልግሎቶችን በየደጁ በማቅረብ ላይ ናቸው፡፡ በዚህም ዘርፈ ብዙና የተቀናጀ ጥረት አማካኝነትም የዜጎች ጤናማነት ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያስረዱት ኢትዮጵያ ለዚህ ውጤት የበቃቸው ያላትን ውስን ኃብት መሰረት አድርጋ ህዝብን ያሳተፈ የጤና ፕሮግራም ስራ ላይ በማዋሏ ነው፡፡ በዓለም አስከፊ ደረጃ ላይ የደረሰውን የጤና ችግር ለመቅረፍ በሚካሄደው ዘመቻ ኢትዮጵያ ምሳሌ ሊሆን የሚችል እመርታ በማሳየት ላይ መሆኗን "Grand Strategy and Global Health" በሚል ርእስ በዚህ ዓመት የወጣ ዘገባ አትቷል፡፡ አገሪቱ ያላትን ውስን ኃብት በመጠቀም ለዘመናት ዜጎቿን ለህልፈትና ለስቃይ ሲዳርጉ የኖሩ በሽታዎችን በከፍተኛ መጠን መቀነስ ችላለች ያለው ይህ ዘገባ አገሪቱ ይህ ስኬት ሊመዘገብ የቻለው መንግስት እያሳየ ባለው የላቀ ቁርጠኝነት ነው ብሏል፡፡

በዚህ ዘገባ ላይ እንደተመለከተው ኢትዮጵያ ውስጥ በወባ በሽታ ምክንያት ህይወቱ ይጠፋ የነበረውን ዜጋ ቁጥር እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ከ2005 ጀምሮ በነበሩት ሶስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ብቻ በግማሽ ቀንሷል፡፡ ይህ ከወባ በሽታ ጋር በተያያዘ በአገሪቱ ያለው የጤና ጠንቅ በአሁኑ ወቅት እጅግ አነስተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን ሰነዶች ያመለክታሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በርካቶችን በከፍተኛ መጠን የሚያጠቁትን የሳንባ ነቀርሳን ጨምሮ የተለያዩ ተላላፊ በሽታዎችን በመከላከል ረገድም ከዚሁ ያልተናነሰ ስኬት አሳይታለች፡፡

ኢትዮጵያን በዓለም ሲያስጠራ የኖረው የእናቶችና የህፃናት ሞት መጠንም በከፍተኛ ደረጃ መቀነሱን በቅርቡ ይፋ የሆነ አንድ ዓለም አቀፍ ጥናት አረጋግጧል፡፡

በትምህርት ዘርፍም ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ስኬት መመዝገቡን ገለልተኛ የሆኑ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጭምር በመመስከር ላይ ናቸው፡፡ ለአያሌ ዓመታት በትምህርት እጥረት ሲማስን የኖረው የኢትዮጵያ ህዝብ በአሁኑ ወቅት በየቀዬውና መንደሩ ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችን ማግኘት ችሏል፡፡ ከ20 ዓመት በፊት አንድም የአንደኛ ትምህርት ቤት ያልነበረባቸው የአገሪቱ ገጠሮች በአሁኑ ወቅት ደጃቸው ላይ ትምህርት ቤት ተከፍቶላቸዋል፡፡

በዚህም አማካኝነት ከ20 ዓመት በፊት እዚህ ግባ ይባል ያልነበረው የአገሪቱ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት አጠቃላይ ሽፋንም ከ96 በመቶ በላይ ልቋል፡፡

ከሁለት አስርት ዓመታት ቀደም በሎ አንድና ሁለት ብቻ የነበሩት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም በአሁኑ ወቅት ከ30 በላይ ሆነዋል፤ እነዚህ ተቋማትም በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን በማስተናገድ ላይ ይገኛሉ፡፡

የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የተከናወኑትን ዘርፈ ብዙ የልማት ጥረቶች ተከትሎ በአሁኑ ወቅት የአገሪቱ ምርታማነት በእጅጉ አድጓል፡፡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት አገሪቱ በየዓመቱ የምትሰበስበው የግብርና ምርት መጠን ከ250 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ደርሷል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም በአገሪቱ በርሃብ ምክንያት ህይወቱ የሚያልፍ ዜጋ የማይታይበት ደረጃን መጎናፀፍ ተችሏል፡፡ በተፈጥሮ አደጋ ሳቢያ ለምግብ እጥረት የሚጋለጡ ዜጎች ቁጥርም በየዓመቱ እያሽቆለቆለ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

ከዚህ የኢትዮጵያ ስኬት ጋር በተያያዘ ዴቪድ ሪፍ የተባሉ ፀሃፊ “Famine and Foreigners: Ethiopia Since Live Aid,” በተሰኘውና በፒተር ጊል በተደረሰው መፅሃፍ ላይ ባቀረቡት የግምገማ ዘገባ ላይ እንዳመለከቱት የኢትዮጵያ የምግብ እጥረት ቀውስ የመከላከል አቅም ተጠናክሯል፤ አገሪቱ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ2003 ገጥሟት ለነበረው ርሃብ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት በየትኛውም ቀደምት የአገሪቱ መንግስት ታይቶ በማይታወቅ መልኩ እጅግ በላቀ ደረጃ ውጤታማ የመከላከል ምላሽ በመስጠት ሊደርስ ይችል የነበረውን የሰብአዊ ቀውስ መታደግ ችሏል፡፡

ሌሎች መሰል አካላትም አገሪቱ የምግብ እጥረትን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ የሚያስችል ተስፋ ሰጪ የልማት ስራዎች በመላው አገሪቱ በማካሄድ ላይ መሆኗን በመግለፅ ላይ ይገኛሉ፡፡

እላይ በተጠቀሱት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስኬቶች ሳቢያም የአገሪቱ የድህነት መጠን ቀንሷል፡፡ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የድህነት መለኪያ (U.N. Human Development Index) መሰረት ኢትዮጵያ ፈጣን መሻሻል እያሳየች ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የአገሪቱ የድህነት መጠን ከነበረበት ወደ .. 29 በመቶ መውረዱንም አገሪቱ ይፋ አድርጋለች፡፡

በቀን አንድ ዶላር የማይሞላ የነበረው የዜጎቿ የነፍስ ወከፍ ገቢም ባለፉት ዓመታት ዓመታዊ ምጣኔው በአማካይ ወደ 370 ዶላር ማደጉን የተለያዩ ጥናቶች አመልክተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለዚህ ስኬት የበቃችው ላለፉት 20 ዓመታት ስራ ላይ ያዋለቻቸው የተለያዩ የልማት እቅዶች ድህነት ተኮር በመሆናቸው፣ ያላትን ውስን ኃብትም ሆነ ከተለያዩ የልማት አጋሮች የሚገኘውን ድጋፍ በአግባቡ በመጠቀሟ ነው፡፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከአንድ ዓመት በፊት ባወጣው ሪፖርት ይህንኑ አረጋግጧል፡፡ የአገሪቱ የልማት አጋር የሆኑት አገራትም ሆኑ ዓለም አቀፍ ተቋማት በተለያዩ አጋጣሚዎች እያረጋገጡት የሚገኘው እውነትም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡

በአገሪቱ ጉብኝት ያደረጉ የልማት አጋሮች በተደጋጋሚ በሰጧቸው አስተያየቶች ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የምትቀበለውን የልማት ድጋፍ ከሌሎች መሰል አገሮች እጅግ በላቀ መልኩ ለተገቢው ዓላማ በተገቢው መንገድ እያዋለች መሆኗን ይገልፃሉ፡፡ ይህንኑ እውነት በተጨባጭ በማረጋገጣቸውም የልማት አጋሮች ሁሉ የሚሰጡትን ድጋፍ አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ቃል ሲገቡም በየጊዜው ይደመጣል፡፡

መንግስት በየዓመቱ በሚያፀድቀው ብሄራዊ በጀቱ ትልቅ ትኩረት ከሚሰጣቸው ሁለትና ሶስት ጉዳዮች መካከል አንዱና ዋነኛው ከምእተ ዓመቱ የልማት ግቦች ጋር ለተያያዙት የልማት ዘርፎች መሆኑም ሌላው ለስኬቱ እንደምክንያት የሚጠቀስ ነው፡፡ ለምሳሌ በቀጣዩ የአገሪቱ በጀት ውስጥ ለምእተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ከ20 ቢሊዮን ብር በላይ መመደቡን ከዚህ አኳያ ማንሳቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

የዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት አንድ የስራ ኃለፊ በቅርቡ በሰጡት አስተያየት በኢትዮጵያ የምእተ ዓመቱን የልማት ግቦች ጨምሮ በተለያዩ ዘርፎች እየተካሄዱ ያሉት የልማትና ኢኮኖሚ ተግባራት አሁን በሚታየው ፍጥነትና ውጤታማነት ከቀጠለ አገሪቱ ከድህነት መውጣት ትችላለች፤ መካከለኛ ገቢ ካላቸው የዓለም አገራት መካከልም ተጠቃሽ ትሆናለች፡፡

አገሪቱ ብሩህ ለሆነው ለዚህ ዓይነቱ ተስፋ ለመጎናፀፍ የበቃቸው በስልጣን ላይ የሚገኘው መንግስት በሚያሳየው የልማት ቁርጠኝነትና በዋናነትም ህዝቡ ድህነትን ለማስወገድ ባደረገው እልህ የተሞላበት ትግል መሆኑን አገሪቱን በቅርበት የሚከታተሉ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ እላይ

**በተጠቀሱትና በተለያዩ አካላት ምስክርነት የተሰጣቸው እውነቶችም የምእተ ዓመቱን የልማት ግቦችን ለማሳካት የተቃረብንበት ሚስጥራት ናቸው፡፡**